“ተነሳ ተራመድ” የቀድሞው
የኢትዮጵያ አየር ኃይል መፅሔት
ሁለተኛ ዕትም - 2017

# የሔሊኮፕተር ምርኰና

## የኛ ሰዎች በአስመራ

ክንዴ ዳምጤ (የበረራ አስተማሪ)



የስራ መውጫ ሰዓት ደርሷል ። ባልተለመደ ሁኔታ ሁለት ኢትዮጵያውያን የበረራ ሙያተኞች ከኤርትራ አየር ኃይል አዛዥ ቢሮ በጥድፊያ ወጥተው ከጭቃ የተሰራች በምትመስልና እንግዳ በሆነች ላንድ ክሩዘር መኪና ተጭነው በፍጥነት ከጊቢው ተፈትልከው ሲወጡ ተመለከትኩ ። ምን ተፈጠረ ? ወዴት ነው ይዘዋቸው የሚሄዱት ? ለምንስ ሁለቱን ብቻ ? በማለት እራሴኑ በጥያቄ አጣድፍኩት ። በዚህ ዓይነት ጥድፊያ እነዚህ ሁለት ሰዎች መወሰዳቸው ከነከነኝ ።

በእርግጥ ከዚህ ቀደም እንዲሁ ሳይታሰብ በአስቸኳይ ትፈለጋላችሁ ተብለን በአካባቢው የነበርነውን ኢትዮጵያውያኖች አየር ኃይሉ አዛዥ ቢሮ የተጠራንበትን ዕለት አስታውሳለሁ ። ያኔ በሻብያና ወያኔ መካከል ግጭት ተፈጥሯል እየተባለ ከዚህም ከዚያም የተለያዩ ተባራሪ መላምቶች የሚናፈሱበት ሰሞን ነበር ። ወደ አስር የምንጠጋ ኢትዮጵያውያን አዛዡ ቢሮ ተገኘተን … “ዛሬ የሰበሰብኳችሁ ሰሞኑን ከግራም ከቀኝም ለሚናፈሰው ወሬ ባይተዋር እንዳትሆኑና ማወቅ የሚገባችሁንም አንዳንድ ጉዳዮች ለማሳወቅ ነው”። ብሎ የኤርትራው አየር ኃይል አዛዥ ኰማንደር ኃብተፅዮን ኻድጉ ንግግሩን ጀመረ ። “ከወያኔ ጋር ከረር ወደ አለ ግጭት ሳንገባ አንቀርም ። ምን አልባትም የከፋ ጦርነትም ሊከሰት ይችላል ። ይሁን እንጂ የቱንም ያክል በደም የተጨማለቀ ጦርነት ቢፈጠር ከእናንተ ዘንድ የሚደርስ ምንም ነገር አይኖርም ። በሰላም የመኖር መብታችሁ እንደተጠበቀ ይቆያል ። እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ይህ ቃሌ አይታጠፍም ። እኔ ከሌለሁ ግን የሚሆነውን ለመገመት እቸገራለሁ ። በእርግጥ ቤተሰቦቻችሁን ጥላችሁ እንጀራ ፍለጋ የመጣችሁ ጓደኞቼና ወንድሞቼ መሆናችሁን በሚገባ አውቃለሁ ፤ የቤተሰብ ፍቅርም ምን ያክል እንደሚጐዳም ይገባኛል ። የቤተሰባችሁ ጉዳይ አሳስቧችሁ ወደ አገር ቤት የመመለስ ውሳኔ ካላችሁ በግል እየመጣችሁ ንገሩኝ ። እኔን ብላችሁ ፣ እኔን አምናችሁ እንደመጣችሁ ሁሉ እኔም ቃሌን በመጠበቅና ውሳኔያችሁን በማክበር በየትም ይሁን በየት መልሼ ከቤተሰቦቻችሁ እንድትቀላቀሉ አደርጋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታውን እዚሁ በመቆየት ለማየት ከወሰናችሁም ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ ከእናንተ የሚደርስ አንዳችም ነገር አይኖርም ፤ ይህ አገር የእናንተም አገር ነውና በሰላም መቆየት ትችላላችሁ ። እንግዲህ ውሳኔያችሁን በግል እየመጣችሁ አሳውቁኝ “። እንዳለን አስታውሰዋለሁ” ። ዛሬ ለምን ሁለቱን ብቻ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይዘዋቸው ሄዱ ? ታፍነው እየተወሰዱ ይሆን እንዴ ? በማለት ነው የተሸበርኩት ።

ከአመት በፊት ሜይ 28 ቀን 1998 ዓም ሻብያ ሁለት የአየር ኃይል በራሪዎችን አፍኖ ወሰዳቸው የሚል ዜና በግል ጋዜጣ ያነበብኩበትን ጊዜ አስታወስኩ ። ጋዜጣውንም ይዤ አዛዡ ቤሮ በመግባት አስነበብኩት ። ለምንና እንዴት ሊታፈኑ እንደቻሉ ምክንያቱን ጠይቆ እንዲነግረኝና እንዲያስለቅቃቸውም አጥብቄ ተማፀንኩት ። አዛዡም ለደቂቃ ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ “እንዲያው አንተ ስታስበው ሻብያ እነዚህን ጁኒየር በራሪዎች በምን ምክንያት ሊያፍናቸው ይችላል ብለህ ታስባለህ ? ዝም ብሎ በየጋዜጣው የተፃፈውን እውነት ነው ብለህ ትቀበላለህ ማለት ነው? በእርግጠኝነት ወያኔ እራሱ አፍኗቸው ዞር ብሎ ደግሞ በጋዜጣ ሻብያ ነው ያፈናቸው ብሎ እንደሚያስወራ አልጠራጠርም ። ሻቢያ እነ ኰ/ል በዛብህ ጴጥሮስንና ሻለቃ ጥላሁን በዛብህን በነፃ አሰናብቶ እነዚህን ወጣት በራሪዎች የሚያፍንበት ምን ምክንያት ይኖረዋል ? ደግሞም በዚህ ላይ ያሳደኳቸው ልጆቼ መሆናቸውን አትርሳ ። ለነገሩ ነገ ከነገ ወዲያ እውነቱን ታውቀዋለህ” ያለኝን ሙሉ ለሙሉ በአዕምሮዬ ከለስኩት ።

ዛሬ ደግሞ ስለ እነ ኰ/ል ማርቆስ ምን ብዬ እንደምጠይቀው እያሰላሰልኩና ልቤ እያመነታብኝ የደመነፍሴን በቀስታ እየተጐተትኩ ወደ ቢሮው ተጠጋሁ ። በሩን ለማንኳኳት እጄን እንደዘረጋሁ ከውስጥ የሰዎች ድምፅ ሰማሁና ባለሁበት ቆምኩኝ ። ለነገሩ ከውስጥ የሚነጋገሩትን ሰዎች በድምፃቸው ለመለየት አልተቸገርኩም ።

ድምፁ ከፍ ብሎ የሚሰማው ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ነበር ። ኰሎኔል ዋቅጋሪ በተፈጥሮው ድምፁን ዝቅ አድርጐ መናገር የማይሆንለት ፣ እንደ ልቡ በነፃነት የፈለገውን የሚናገር ሰው መሆኑን ከድሮም አውቃለሁ ። ሲበዛ ቅንና የዋህ ሰው ነው ።

ሁለተኛው በሳቁ የለየሁት ሰው ደግሞ ዶ/ር ኤፍሬም ይባላል ። ሰውነቱ ሁሉ እስኪንዘፈዘፍ ድረስ ስለሚስቅ አሳሳቁ በዙርያው ያሉትን ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲስቁ ያደርጋቸዋል ። ጨዋታ ወዳጅ ፣ ለጓደኞቹ ልዩ ፍቅር ያለውና ለመዝናናት ሙት የሆነ ሰው ነው ።

ዶ/ር ኤፍሬም ፍሰሃን አስመራ እስከማገኘው ድረስ የጅማ ልጅ አድርጌ ነበር የምቆጥረው ። በእርግጥም ተወልዶ ያደገው ጅማ ነው ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ የአቪዬሽን ዶ/ር ሆኖ ሲያገለግል አውቀዋለሁ ። ከሁሉም የአየር ኃይል አባላት ጋር ጥሩ ግንኙነት የነበረውና ከትንሹም ከትልቁም ጋር አብዝቶ ተግባቢ ሰው ነው ። በስራም ሆነ በግል ጉዳዮች በተደጋጋሚ የተገናኘን በመሆኑ ከመግባባት የዘለለ ጥሩ እውቂያ ነበረን ። በአሁኑ ሰዓት በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ የአቪዬሽን ዶ/ር ሆኖ እየሰራ ይገኛል ። ያው እንደ ድሮው ከኢትዮጵያውያኖች ጋር እጅግ የቀረበ ወዳጅነትና መግባባት አለው ።

ከውስጥ የሚሰማውን ድምፅ ለመለየትና የአዛዡን ቢሮ ለማንኳኳት ሳልደፍር ደፉ ላይ እንደቆምኩ በሩ ድንገት ተከፈተና ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተያይዘው ከቢሮ ወጡ ።

አዛዡ ኰማንደር ሃብተፅዮን ሃድጐ- በቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮን ውስጥ ሲያገለግል የነበረና በ1990 መጀመሪያ ላይ አውሮፕላን ይዞ የመን የገባ ሲሆን ከመንግስት ለውጥ በኋላ የኤርትራ አየር ኃይል አዛዥ ሆኖ እያገለገለ ነው።

ኰ/ል አብርሃም ዕቁባ ስላሴ- ቀደም ሲል በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በበራሪነት ሲያገለግል ቆይቶ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ተዛውሮ ሲሰራ የነበረና ከመንግስት ለውጡ በኋላ ወደ ኤርትራ በመምጣት አየር ኃይሉ ውስጥ ም/አዛዥ ሆኖ ይሰራል።

ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ የወለጋ ሰው ነው ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮኖች ውስጥ ሲያገለግል የነበረና ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ኢትዮጵያውያን በራሪዎች መካከል አንዱ ነው ። ከመንግስት ለውጥ በኋላ በስደት ኬንያና ኡጋንዳ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*ሲኖር ቆይቶ በአሁኑ ሰዓት ኤርትራ ውስጥ እየኖረ ነው ።*

*ኰ/ል ታደሰ ሙሉነህ ተወልዶ ያደገው ባህር ዳር ነው ። እንደ ኰ/ል ዋቅጋሪ ሁሉ በኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ ስኳድሮን ውስጥ ከፍተኛ ልምድ ያለው በራሪ ነው ። ከመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ ኤርትራ በመምጣት በአየር ኃይሉ ውስጥ በበረራ አስተማሪነት እያገለገለ ያለ ነው ። አብሯቸው ዶ/ር ኤፍሬም ፍሰሃም አለ ።*

*ከሁሉም ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ኰ/ል ታደሰ ገንጠል ብሎ ወደ እኔ በመጠጋት ወዴት ነህ ? … እንሂድ እንጂ አለኝ ። የስራ መውጫ ሰዓት በመድረሱ ወደ ቤት እንሂድ ማለቱ ነበር ፤ ልቤ ነገር እንዳረገዘ እሺ ብዬው ተከተልኩት ።*

*ከኰ/ል ታደሰ ጋር ወደ መኪና ውስጥ ልንገባ ስንል ኰ/ል ወቅጋሪ ገመቹ ድምፁን ከፍ በማድረግ ባለቤቴን ወደቤት አድርሺያት ቶሎ እመለሳለሁና ቱሉ ጋ ጠብቁኝ በማለት እየተጣደፈ ወደ አየር ኃይል ሆስፒታል አቅጣጫ ባለቤቱን ዶ/ር ሊያ ጋቢሳን ሊያነሳ ሲሄድ እኛም ወደ ቤት መሄዱን ትተን ቱሉ ወደ ሚገኝበት አቅጣጫ አቀናን ።*

*የኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ባለቤት ዶ/ር ሊያ ጋቢሳ ይባላሉ ። በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ እስከ መንግስት ለውጥ ድረስ በሃኪምነት ሲያገለግሉ ነበር ። ከ1998 ዓም በኋላ ግን እዚህ አስመራ በመምጣት በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ እንደቀድሞው በሃኪምነት እየሰሩ ነው ።*

*ከኰ/ል ታደሰ ጋር ወደ ከተማዋ አቅጣጫ መንዳት እንደጀመርን ትኩር ብሎ እየተመለከተኝ ምን ነው ? ምን ሆነሃል ? ችግር አለ እንዴ ? ብሎ አከታትሎ ጠየቀኝ ። በውስጤ የቋጠርኳትን ነገር ፊቴ ላይ እንዳነበበ ገባኝ ። ፈጥኜም እነ ጂሚን ከአዛዡ ቢሮ አውጥተው እያጣደፉ ጮቃ በመሰለች መኪና አሳፍረው ሲወስዷቸው አይቼ ጉዳዩ አሳስቦኝ ነው አልኩት ። ሁኔታውን በተመለከተም የሚያውቀው ነገር እንዳለ አክዬ ጠየቅኩት ። ማ/ቴክ ግርማ ለማን "ጂሚ" በሚል የቅፅል ስያሜ እንጠራዋለን ። ከ1991 የመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ አስመራ በመምጣት በኤርትራ አየር ኃይል ሄሊኮፕተር ስኳድሮን ውስጥ በበራሪ ቴክኒሻንነት እያገለገለ ያለ ከፍተኛ ልምድ ያለው መካኒክ ነው ።*



**ካቴድራል - አስመራ**

*ጥያቄዬን እንደጨረስኩ አንዳች ነገር ትዝ እንዳለው ሁሉ .. እእ .. በማለት ጀመረ ኰ/ል ታደሰ ። አስከትሎም እነ ጂሚማ ወደ ባድመ ዘምተዋል በማለት ፊቱን ወደ እኔ እየመለሰ ፈገግ ብሎ መለሰልኝ ።*

*ፈገግታውን አልወደድኩለትም ፣ በደምብ ያላዳመጠኝና ያልተረዳኝም እንዲያውም የሚያሾፍብኝ መሰለኝ ። እናም ድምፄን ከፍ በማድረግ … እውነቴን እኮ ነው ፤ በሆነ መኪና ጭነው ወስደዋቸዋል እያልኩህ ነው በማለት ቆጣ ብዬ ስጋቴን ደገምኩለት ። ነገሩን እንዳላጤነውና እንዳልገባው ሁሉ ።*

*እኔም እውነቴን ነው ። ባድመ አካባቢ አንድ ሚ-35 ወድቃ ተገኝታ እሷን ለማምጣት ወደዛ ዘምተዋል አለኝ … ከረር ባለና እርግጠኛ በሆነ ድምፅ ።*

*ጭራሽ አሁን የባሰውን ግራ ገባኝ ። እንዴት ነው ሄሊኮፕተር ወድቆ የሚገኘው ? ዛሬ ደግሞ ሔሊኮፕተር እንደ ሳንቲም መሬት ወድቆ ይገኝ ጀመር እንዴ ? ለመሆኑ መቼ ነው ወድቆ የተገኘው ?*

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የትስ ነው የተገኘው ? ፓይለቶቹስ የት ገቡ ? በማለት መላ ቅጡ የጠፋውን ጥያቄን አከታትዬ ደረደርኩለት ።

ኰ/ል ታደሰ እንደተምታታብኝና እንደ አመረርኩ በመገንዘብ … ባድሜ ግምባር .. ማይድማ ከሚባል አካባቢ ነው አሉ አለኝ ፤ መቀለዱን በማቆም ። ሄሊኰፕተር ማርከናል ነበር የተባለው ፤ እኔ ግን ክሩዎቹ (የአውሮፕላኑ ሰራተኞች) ስላልተገኙ ነው ወድቆ ተገኝቷል ያልኩህ በማለት ግልፅ ሊያደርግልኝ ሞከረ ። ከዚህ ውጪ ብዙ ዝርዝር ነገሮችን አልሰማሁም ፤ ለማንኛውም ነገ ከሄዱበት ሲመለሱ ሁሉንም እንሰማዋለን አለኝ በረዥሙ እየተነፈሰ ።

የማይመስል ነገር ነው ! አልኩት ነገሩን በማጣጣልና ጥርጣሬ ውስጤ እንደተቀበረ በሚገልፅ ቅላፄ ። እየነገረኝ ያለውን ታሪክ ለማመን እየተቸገርኩ ።



ሚ-35 ተዋጊ ሔሊኰፕተር

ጦርነት እኰ ነው ! አለኝ በጩኸት ንግግሬን አቋርጦ ። አስከትሎም የጦር መሳሪያ ወድቆ ልታገኝ ትችላለህ ፣ ታንክ ልትማርክ ትችላለህ ። ሔሊኰፕተርም እኰ የጦር መሳሪያ ማለት ነው ። በጦርነት ላይ ምንም ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ አለብህ ፤ ምኑ ነው ያስደነቀህ ? … አለኝ ። በጉዳዩ ብዙም ሳንግባባና የመንገዱም ርዝመት ሳይታወቀን ቱሉ ዘንድ ደረስን ።

ቱሉ ሁልጊዜ ሲያገኘን ይደሰታል ። እንደ ወንድሞቹም ይመለከተናል ። እኛም እሱን ለመጠየቅ ስንል አዘውትረን ወደ እሱ ጋ ጐራ እንላለን ። እናንተን ሳገኝ ውስጤን ደስታ ይሰማዋል ይለናል ።

ቱሉ ሰላሌ ተወልዶ ያደገ ለግላጋ ወጣት ነው ። በእናቱ ወይም በአባቱ ከኤርትራ በመወለዱ ምክንያት የሻብያና ሕውሃት ግጭት እንደተጀመረ ከኢትዮጵያ ተባረረ ። የኤርትራን ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጠው ከኢትዮጵያ ተባሮ የመጣ ጊዜ ነው ። ትግሪኛ ጆሮውን ቢቆርጡት እንኳ አይሰማም ። እሱ እንደሚለው ከሰላሌ ፈፅሞ ወጥቶ አያውቅም ።

ከሁሉም የተቸገረበት ጉዳይ ማንም በኤርትራዊነት ሊቀበለው ያለመቻሉ ነው ። አብዛኛው ኤርትራዊ ቱሉ እባላለሁ ብሎ ሲተዋወቃቸው የሚያሾፍባቸው እየመሰላቸው ከት ብለው ይስቁበታል ። ቱሉ ብሎ ኤርትራዊ እያሉ ፊት ለፊት ይሳለቃሉ ። ቱሉ ታድያ በእጅጉ ያዝናል ። ይኼኔ ተወልዶ ያደገባትን ሰላሌን ይናፍቃል ፣ የሚወዳትን ሰላሌን ተነጥቋልና ይቆጫል ።

ቱሉ ዘወር ሲልልን እኔና ኰ/ል ታደሰ ቀደም ብለን ወደ አቋረጥነው ጨዋታችን በመመለስ “የሚወራው እውነት ከሆነ ሻብያ አንድ ተዋጊ ሄሊኰፕተር ቀናው ማለት ነው” አለኝ ኰ/ል ታደሰ በሹክሹክታ ። አያይዞም “አየህ ባለሙያን አክብሮ መያዝ ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው ። ኰ/ል ማርቆስ እዚህ ኤርትራ መኖር ባይችል ኖሮ ይህቺን ባድመ ላይ ወድቃ ተገኘች የተባለችውን ሄሊኰፕተር ለማምጣት በዚህ ፍጥነት ማን ይሄድ ነበር አለኝ ?” በወቅቱ ድፍን ኤርትራ ቢታሰስ ተዋጊ ሔሊኰፕተሮችን ለመብረር ከኰ/ል ማርቆስ ውጪ ሌላ ብቁ በራሪ ያለመኖሩን በመገንዘብ ።

“አየህ ባለሙያ ወርቅ ማለት ነው ። በክፉ ቀን ይጠቅምሃል ። ለዚህም ነው ሃገር ከፍተኛ ሃብት እያፈሰሰች የምታስተምራቸው ። ሃብተፅዮን የባለሞያን ጥቅም ስለሚያውቅ በቀላል ወጪ ተገቢውን ሙያዊ ክብር እየሰጠን አዲሱን አየር ኃይላቸውን እንድንገነባ ያደርጋል” ። በማለት በአገራችን ሁኔታ እየተቆጨ ነገረኝ ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እኔና ኰ/ል ታደሰ በዚህ ጉዳይ ሞቅ ያለ ጨዋታ ውስጥ ሰጥመን ሳለን ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ እየተጣደፈ በመግባት ድምፁን ከፍ አድርጐ ቱሉን በኦሮምኛ ሲያናግረው ሰማን ።

“ አካም ጅርታ ቱሉ ” ...... ። ቱሉ እናቱ የመጣችለት ያክል ፊቱ ሁሉ ጥርስ በጥርስ ሆኖ ወደ ኰ/ል ዋቅጋሪ በመጠጋት በደስታ ይፍነከነክ ገባ ። በላይ በላዩ እየተጣደፈ ኦሮምኛውን ያስኬደው ጀመር ። ሁለቱም ከጣሪያ በላይ ይስቃሉ ።

የኰ/ል ዋቅጋሪ በራስ መተማመን የሚገርም ነው ። በኦሮምኛም በአማርኛም .... ሲያሰኘውም ትግሪኛም እየቀላቀለ ድምፁን ከፍ አድርጐ ይጫወታል ። ለእርሱ አዲስ አበባም አስመራም ... መቀሌም ሆነ ለቀምት ልዩነት የላቸውም ። እንደልቡ ድምፁን ከፍ አድርጐ በፈለገው ቋንቋ መናገር ያደገበትና የኖረበት በመሆኑ ዕከሌ ምን ይለኛል ብሎ አይሸማቀቅም ። ቱሉም ለዚህ ይመስለኛ የመሃል አገር ሰዎችን በሩቅ ሲመለከት በደስታ የሚፍነከነከው ።

ይኼኔ ጥሩ አጋጣሚ ስለአገኘሁ ፊቴን ወደ ኰ/ል ዋቅጋሪ መልሼ “ ጌታዬ .. መጀመሪያ አስመራ ከእነ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ጋር ያገኘሁህ ጊዜ እኰ በኦነግነት አምተንህ ነበር ” አልኩት ። ያኔ እንዳየሁት ወደ ቤቴ ሄጄ ለኰ/ል ግርማ ጫላ ኰ/ል ዋቅጋሪን ከእነ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ጋር ቆሞ አየሁት ብዬው የነገርኩትንና ኦነግ ሆኖ መጥቶ መሆን አለበት ብለን ያማነውን በማስታወስ ።

ንግግሬ ያስቆጣው ኰ/ል ዋቅጋሪ በብስጭት ቱግ ብሎ “ ምነው ባክህ ? አየር ኃይል እኰ ነው ያሳደገኝ ... ተማሪ ሆነን እንኳ ዶርሚተሪያችን (መኝታ ቤታችን) ቤኔምድር ፣ ወለጋ ፣ ወሎ ... ነው እንጂ ኦሮሞ .. አማራ የሚል ስያሜ አልነበረውም ። እንዴት እዚህ ድረስ ዝቅ አድርገህ ትገምተኛለህ ? እኔ እኰ ከአየር ኃይል ጋር የኖርኩ ፣ በዘር ዘምቢል ውስጥ ገብቼ ልኖር የማልችል ባለ ሰፊ ማህበረሰብ አካል ነኝ ” አለኝ ከልቡ ውስጡን እየተሰማው ። ለነገሩ እኔም ይህንን አውቃለሁ ። አየር ኃይል ከመላው አገሪቷ እየዘረ የሚያመጣቸውን አዲስ ምልምሎች በሶስት ወራት ስልጠና ብቻ እንዴት አድርጐ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሆነ ብሄራዊ መንፈስ እንደሚቀርፅና ከአንድ እናት የተፈጠርን ወንድማማች አድርጐ እንደሚያወጣን በውስጤ እየመሰከርኩ ። እናም ጥፋተኝነት ተሰምቶኝ ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ ኰ/ል ዋቅጋሪን ይቅርታ ጠየቅኩት ።

በመንግስት ለውጡ ሳቢያ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሙሉ ለሙሉ እንዲበተን ከተፈረደበት በኋላ ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ሰኔ 1998 ዓም አስመራ አየር ኃይል ቤዝ ውስጥ ከፕሬዝዳንት ኢሳያስና ከጀ/ል ስብሃት ኤፍሬም (የኤርትራ የመከላከያ ሚንስትር) ጋር ቆመው ሲያወሩ ነበር ። ሰላም ለማለት ሶስቱ ወደቆሙበት አቅጣጫ ስጠጋ ድንገት ያስተዋለኝ ኰ/ል ዋቅጋሪ አፉን በመዳፉ እየሸፈነ በመደነቅ “አንተም ኤርትራዊ ነህ ” ? ያለኝ ምንግዜም አይረሳኝም ። ድሮ አብረን ስንኖር የቱ ከኤርትራ የትኛው ደግሞ ከትግሬ እንደሆነ ለመለየት ግድ እንደሌለን በሚያስታውቅ ቅላፄ ።

“የለም ጌታዬ ፤ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ፤ እዚህ ኤርትራ ለስራ መጥቼ ነው” በማለት ሶስቱንም በየተራ ጨበጥኳቸው ። “አሃ! እንደ እነ ኰ/ል ታደሰ ነሃ” ብሎኝ በሌላ ጊዜ በሰፊው እንደምንገናኝ ገልፆልኝ እንደተለየኋቸው አስታውሳለሁ ።

ኰ/ል ዋቅጋሪ ኢህአዴግ አገሪቷን እስኪቆጣጠር ድረስ የሶስተኛው አየር ምድብ (ድሬዳዋ ቤዝ) አዛዥ ነበር ። በመጨረሻዋ ደቂቃ ከሌሎች በራሪዎች ጋር በአንቶኖቭ 12 አውሮፕላን ወደ ኬንያ ይሰደዳል ። ከኬንያም ወደ ኡጋንዳ በመሸጋገር በኡጋንዳ አየር ኃይል ውስጥ በበራሪነት አግልግሏል ። ሙያውን እየሸጠ ጥሩ ገቢም ነበረው ። በዚህ ላይ ባለቤቱም የሕክምና ዶ/ር በመሆኗ ኑሯቸው ከጥሩ በላይ ነበር ።

ከሰባት ዓመታት የኡጋንዳ ኑሮ በኋላ ኤርትራና ሕውሃት ወደ ግጭት ሲያመሩ ሕውሃቶች ቀርበው ሊያግባቡት ሞክረዋል ። “ አገራችን በባዕዳን ተወራለችና ይህንን የድፍረት ወረራ ልዩነታችንን በማቻቻል አብረን እንመክት ” ይሉታል ። አገር የመከላከሉን ጉዳይ ኰ/ል ዋቅጋሪ አልጠላውም ። ነገር

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሳቱ ከሕውሃት ተወካዮች ጋር ሊግባባ አልቻለም ። ወደዚህ ወደ ኤርትራም ለሶስተኛ ጊዜ እንዲሰደድ ያደረገውም ይኸው የሕውሃቶች ትንኰሳ እንደሆነ ይናገራል ።

ኰ/ል ዋቅጋሪ እኛን ተቀላቅሎ እንደተቀመጠ ወድቃ ተገኘች በተባለችው ሔሊኰፕተር ዙርያ ስለ ኰ/ል ማርቆስና ማ/ቴክ ግርማ ጉዳይ መነጋገራችንን ቀጠልን ።

ኰ/ል ማርቆስ ሰለሞን በቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በሔሊኰፕተር ስኳድሮን ውስጥ ታዋቂና ከፍተኛ ልምድ ያለው በራሪ ነበር ። ተወልዶ ያደገው ሐረር ውስጥ ከወታደር ቤተስብ ነው ። በኋላም ሐረር የጦር አካዳሚ በመግባት በመኰንነት ተመርቆ መጀመሪያ በአርሚ አቭዬሽን ውስጥ ቀጥሎም በኢትዮጵያ አየር ኃይል የተለያዩ ስኳድሮኖች ውስጥ በበራሪነት አገልግሏል ። በ1991 የመንግስት ለውጥ እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በራሪ በአዲሱ ስርዓት በሌሉበት የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው በራሪዎች ውስጥ ይካተታል ። በስደት ወደ ኤርትራ በመምጣትም በኤርትራ አየር ኃይል ውስጥ በሔሊኰፕተር በራሪነትና በአስተማሪነት እያገለገለ ይገኛል ።

እነሆ ዛሬ በባድመ ግምባር ማይድማ አካባቢ አንድ ሔሊኰፕተር ወድቃ ተገኝታለች መባሉን ተከትሎ ወደ ባድመ በመሄድ ሔሊኮፕተሯን ለማምጣት መዝመታቸውን ኰ/ል ታደሰ እየነገረን ቢሆንም እንዴት ተበላሽታ የወደቀች ሔሊኰፕተርን አስነስተው ሊያመጡ ይችላሉ ? በማለት ግራ እያጋባኝ ያለውን ጉዳይ ጠየቅኩ ።

ኰ/ል ዋቅጋሪም ሃሳቤን በመቀበል ሌላ ተጨማሪ ስጋት ይሆናል ያለውን ሃሳብ ሰነዘረ ። “እንዲያው የፈለገውን ያክል የዘመኑን የአየር ኃይል ኃላፊዎች አሳንሰን ብናያቸውም ይህቺን ሔሊኰፕተር ለጠላት አሳልፈው የሚሰጡ አይመስለኝም ፤ በፍጥነት ያለችበት ድረስ በመሄድ ለማውደም መሞከራቸው አይቀርም ። በዚህ ላይ አጠቃላይ ዘመቻውን በመምራትና በአማካሪነት እያገለገሉ ያሉት ብ/ጄ ተጫኔ መስፍን መሆናቸውን አንርሳ ። ጀ/ል ተጫኔ ሔሊኰፕተሯን ማውደም እንደሚገባ የሚጠፋቸው መኰንን አይደሉም ። ስለዚህ ይህ ዘመቻ ለእነ ኰ/ል ማርቆስ አደገኛ ሊሆን ይችላል በማለት ስጋቱ ገለፀ ።




ጄ/ል ተጫኔ መስፍን ወሎ ኰረም ነው እድገታቸው ። ኰረም ይደጉ እንጂ መሰረታቸው ግን አድዋ እንደሆነ ከለውጡ በኋላ ጮክ ብሎ መነገር ጀምሯል ። በፈረጆቹ 1955ዓም አየር ኃይልን ተቀላቅለው በተለያዩ ተዋጊ ስኳድሮኖች ውስጥ በተዋጊ በራሪነት ካገለገሉት ምርጥ በራሪዎች ውስጥ አንዱ ለመሆንም በቅተዋል ። በጀ/ል ማዕረግ ወደ መከላከያ ሚንስቴር ተዛውረው በዘመቻ መምሪያ ውስጥ ለበርካታ አመታት ሰርተዋል ። ኢህአዴግ አገሪቷን እስኪቆጣጠር ድረስ ዘወትር ማለዳ ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት መኪናቸውን እራሳቸው እያሽከረከሩ በጀት በረራ ማሰልጠኛ ስኳድሮን ውስጥ እኔን ጨምሮ ተዋጊ በራሪዎችን ያስተምሩ የነበሩ ጠንካራ የአየር ሰው ናቸው ። በተዋጊ ጀት አውሮፕላን በራሪነት ያከማቹት ሰዓት በአፍሪካ አህጉር ሻምፒዮናነቱን እንደያዙ እንዲቆዩ አድርጓቸዋል ። ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣ ማግስትም ወደ ወህኒ ተጥለው ለሰባት ዓመታት ከርቸሌ ተከርችሞባቸዋል ። በ1998 ዓም በሻብያና ወያኔ ግጭት ሳቢያ ከሌሎች አቻዎቻቸው ተለይተው ከእስር የመፈታታቸው ሚስጢር እንደተከደነ ቢቆይም በአየር ኃይል ዘመቻ መምሪያና በዘመቻ አማካሪነት እያገለገሉ ናቸው ።

ይህንን የጀ/ል ተጫኔን ዕምቅ ልምድ ነው ኰ/ል ዋቅጋሪ የፈራው ። እኚህ የተዋጣላቸው የአየር ኃይል

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ባለሙያ አማካሪነት አይደለም አየር ኃይሉን እራሱን የማዘዝ ብቃት አላቸው እያለን ነው ፤ ኰ/ል ዋቅጋሪ ። ስለዚህ የእነ ኰ/ል ማርቆስ ወደ ባድመ የመዝመቱ ጉዳይና ወደቀች የተባለችውን ሔሊኮፕተር ወደ አስመራ እየበረሩ የማምጣቱ ጉዳይ የሚሳካ እንዳልሆነ በዝርዝር አወጋን ።

አያይዘም "ጀ/ል ተጫኔ ከእስር ተለቀው በዘመቻ አዛዥነትና በአማካሪነት መመደባቸውን የሰማሁ ግዜ ለምን እሳቸውን ብቻ ከእስር ፈቷቸው የሚለውን ጥያቄ ቢያጭርብኝም ወደ አየር ኃይል በመመለሳቸው ተደስቼ ነበር አለን ። በእሳቸው ግፊት ሁኔታዎች ይሻሻላሉ ብዬ ተስፋ በማድረግ ወደ አገር ቤት ለመመለስም አስቤ ነበር ። የታሰሩት ይፈታሉ ፣ የተሰደዱትም ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ። አየር ኃይልም ወደ ነበረበት ተመልሶ ለአገር ጠቃሚ እንደሆነ ይቀጥላል ። ቂምና በቀልም ያከትማል ብዬ ሙሉ ለሙሉ አስቢያለሁ ። ስለ አገራችንም ሆነ ስለ አየር ኃይል በአዲሶቹ መሪዎች በኩል የተሻለ ግንዛቤ አግኝቶ ... ሁላችንም አገራችንን የምናገለግልበት ሁኔታ ይመቻቻል እያልኩ ነበር ።

የሕውሃት ሰዎች በስደት የምኖርበት አገር ድረስ መጥተው "አገራችን ተወራለች ፣ ዳር ድንበራችንም ተደፍሯል .. ልዩነታችንን አስወግደን አገራችንን በጋራ መከላከል አለብን ብለው ሲያነጋግሩኝ መጀመሪያ ፈቃደኛ ሆኜ ነበር ። "በኋላ ግን አንድ ጥያቄ አቀረብኩላቸው ። "እዚህ ድረስ እኔን መጥታችሁ እንዳናገራችሁኝ ሁሉ እዚያው አገር ውስጥ በእስር ላይ ያሉትንስ ጠይቃቹኋቸዋል ወይ? "ብዬ ጠየቅኳቸው ። ይህንን ጉዳይ ጀ/ል ተጫኔም እንደሚያነሱባቸው እየተማመንኩ ።

"አይይይ ... አገር ውስጥ በእስር ላይ የሚገኙት የአየር ኃይል ሙያተኞች እኮ በቀይ ሽብር ጉዳይ ተከሰው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ያሉ ሰዎች ናቸው" ብለው ሲመልሱልኝ እንደዋሹኝና ተንኰል እንዳለበት ስለገባኝ ወደ አገር ለመመለስ ያለኝን ሃሳብ ቀየርኩኝ ።

"በአገር ውስጥ በእስር ላይ ያሉት የአየር ኃይል አባላት አብዛኛዎቹ ጓደኞቼ ናቸው ። ከአየር ኃይል ስራ ውጪ ከቀይ ሽብር ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ጉዳይ እንደሌለ እራሴን የማውቀውን ያክል አውቃቸዋለሁ ። ስለዚህ ነገሩ ሁሉ አላምር አለኝ ። ጓደኞችህ በቀይ ሽብር ተከሰው ነው ከርቸሌ የወረዱት የሚለውን የውሸት ክስ አምኜ ወደ አገር ከምመለስ ብሞት ይሻለኛል ብዬ የአብሮ እንስራ ጥያቄያቸውን ሳልቀበክ ቀረሁ። አለን ኰ/ል ዋቅጋሪ ።

አያይዘም በጄ/ል ተጫኔ እስከ መጨረሻው ተስፋ አለኝ ። የብቀላውን ክስ ያስቀለብሳሉ ፣ በግፍ እስር ቤት የሚማቅቁትን ጓደኞቻችንና በሌሉበት የሞትና የዕድሜ ልክ ፍርደኞችን ነፃ እንዲወጡ ይጥራሉ ብዬ አስባለሁ ። ይህንን ሳይፈፅሙ ቀርተው በወገንተኝነት ከህውሃት ጋር በመስራት የሚዘልቁ ከሆነ ግን እንተዛዘባለን" ብሎን በረዥሙ ተነፈሰና ወጉን ጨረሰ ።

እንደ ፈራነው ሳይሆን በነጋታው ጠዋት ከስራ መግቢያ በፊት የባድሜዋ ሔሊኮፕተር በቀድሞው ባለቤቶቿ አማካኝነት አስመራ አየር ማረፊያ በሰላም ደረሰች ። በፍፁም ሊታመን የማይችል ነው ። ያለ እንከን እየሰራች ያለች ሄሊኰትተር ለጠላት ጥሎ መሄድ ምን የሚሉት ችሮታ እንደሆነ መገመት አቃተኝ ። ሄሊኰፕተሯን መብረር ባይቻል እንኳ ጠላት እጅ ገብታ መጠቀሚያ እንዳትሆን ማውደም ማንን ገደለ ? በአለም የምርኮ ታሪክ የዚች ሄሊኰፕተር ጉዳይ የመጀመሪያው መሆን አለበት ። እንዲሁ እንቅልፍ እንዳጣሁ ስገላበጥ አድሬ ንጋት ላይ ገና ሸለብ እያደረገኝ በነበረበት ሰዓት ነው የሄሊኰፕተር ድምጽ በመኖሪያችን አናት ላይ ሲያልፍ የሰማሁት ። ዘልዬ ከአልጋዬ ላይ በመነሳት ወደ አየር ኃይል ግቢ አመራሁ ። በረራ መስመር ስደርስ አዛዡን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ሄሊኰፕተሯን ከብበው በአሽናፊነት ያውካካሉ ።

ኢትዮጵያዊው የአርማሜንት (የጦር መሳሪያ) ስፔሺያሊስት ማ/ቴክ አርጃ ጴራ በደቂቃዎች ውስጥ ሄሊኰፕተሯ የታጠቀችውን መሳሪያ ሁሉ ፈታትቶ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መሬት ላይ ዘርግፎታል ። ሄሊኮፕተሯ ጥይትና ሮኬት ታጥቃ ነበር ። ውስጤ ሲሸማቀቅና የመዋረድ ስሜት አንገቴን ሲያስደፋኝ ይታወቀኝ ነበር ። እንዴት እንደዚህ አይነት ስህተት ይሰራል ? በምንስ ምክንያት ይህቺን ሄሊኮፕተር ባለችበት ማውደም ከባድ ሆነ ? እጅግ አሳፋሪ ሆኖ ተሰማኝ ።

የኤርትራ አየር ኃይል አዛዡ ወደ ሔሊኮፕተሯ ኮክፒት ውስጥ በመግባት ያገኛቸውን ቁሳቁሶች ይዞ ወረደ ። በራሪዎቹ ጥለውት የወረዱትን ፎቶ ግራፎች በእጁ ይዟል ። የማውቃቸው ጓደኞቼ ናቸው ። ከፎቶ ግራፎቹ መካከል የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ዜጎችም ይገኙበታል ። በዚህኛውም ወገን አስመራ ያሉት የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ዜጎች በፎቶ ግራፉ ላይ የሚመለከቷቸውን በራሪዎች ያውቋቸዋል ። አለም እንደዚህ ናት ። በዚህም ወገን ሆነ በዚያኛው ወገን በገንዘብ የተገዙ ጓደኛሞች ኖረዋል ጦርነቱን የሚዋጉት ።

የኤርትራው አየር ኃይል አዛዡ የደስታና የአሸናፊነት ስሜት ጐልቶ ይንፀባረቅበታል ። ኰ/ል ማርቆስንና ማ/ቴክ ግርማን እያቀፈ አድናቆቱን ይለግሳቸዋል ።

ሄሊኮፕተሯን እየዞርኩ ስመለከት ከሆዷ ስር ዙ-23 በሚመስል ጥይት መመታቷን አስተዋልኩኝ ። ጥይቱ የነዳጅ መስመሩን ጐድቶት ኖሮ ነዳጅ እየፈሰሰ እንደነበረ በሚገባ ያስታውቃል ። ለሄሊኮፕተሯ መውደቅ ምክንያት የሆነው በአየር ላይ ሆና ከምድር በተተኰሰ የአየር መቃወሚያ መመታቷ እንደሆነ ተገነዘብኩኝ ።

በኋላ ግን ኰማንድ ፖስትና ጠቅላይ መምሪያ በአዛዥነት ተቀምጠው ጦርነቱን የሚመሩትን ሰዎች አምርሬ ረገምኩ ። እንዴት እንደዚህ አይነት ስህተት በመስራት በአየር ኃይል ስሟ የገነነውን አገር ያዋርዳሉ ብዬ ወቀስኳቸው ። ሄሊኮፕተሯን ያለችበት ሄደው እንድትወድምና ጠላት እጅ እንዳትገባ ማድረግ ነበረባቸው ። የዚህ ሁሉ ዝብርቅርቅ ክስተት ተጠያቂ ማን ነው ብዬ ሳስብ ሙያዊ ብቃት በሌላቸው ሰዎች የመመራቱ ጦስ እንደሆነ ደመደምኩ ። ሙያና ባለሙያ እንዲለያዩ ተደርጓል ። ኢትዮጵያ አገራችን በአፍሪካና በዓለም ደረጃ የነበራትን የአየር ኃይል ብቃት በማዋረድ በኲል ሌት ተቀን ተሰርቷል ።

በዚህ ሁኔታ አገር ሊገነባ እንደማይችል ግልፅ ነው ። ለዘመናት የአገር ኃብት የፈሰሰበትን ባለሙያ በአንድ ጀንበር አውድሞ ለባዕዳን ገፀ በረከት እንዲሆኑ ማድረግ አገርንም ሕዝብንም እንደሚጐዳ እያየነው ነው ።



ሚግ-21 ስኳድሮን ፣ አሥመራ

ኰ/ል ዋቅጋሪ ፣ ኰ/ል ታደሰ ፣ ኰ/ል ግርማ ፣ ኰ/ል ማርቆስ ፣ ማ/ቴክ ግርማ ፣ ማ/ቴክ አርጀ ….. ስንቱን ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ቆጥሬው እንደምዘልቀው አላውቅም ። ግን እነኚህ ሁሉ አገራችን በሚያስፈልጓት ሰዓት በክፉ ቀን ያልሆነ ቦታ ላይ የተገኙ ናቸው ።



ኰ/ል ዋቅጋሪ ገመቹ ከባለቤታቸው ከዶ/ር ሊያ ጋቢሳ ጋር

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com